በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1995 በጀት ዓመት
# የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም
# ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1995

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1995 በጀት ዓመት
## የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም
## ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1995

# ማ ው ጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| 2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ | 2 |
| 2.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት | 2 |
| 2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት | 5 |
| 2.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት | 6 |
| 2.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት | 7 |
| 3. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ | 10 |
| 3.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ | 10 |
| 3.2 የመዛግብት አያያዝ ስታንደርድን በተመለከተ | 10 |
| 4. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ | 11 |
| 5. ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት | 11 |
| 6. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት | 12 |
| 7. የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት | 13 |
| 8. የኦዲት አገልግሎት | 14 |
| 9. የሕግ አገልግሎት | 14 |
| 10. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት | 14 |
| 11. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና | 15 |
| 11.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ | 15 |
| 11.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ | 16 |
| 12. የበጀት አጠቃቀም | 17 |
| ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም | 17 |
| ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም | 18 |
| 13. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት | 20 |
| 14.1 ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል | 20 |
| 14.1 ትራንስፓርትና ጥገናን በተመለከተ | 20 |
| 14.2 ሕትመት | 21 |
| 14. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች | 21 |

# የ1995 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት
# የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችን ለማስፈፀም የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ለማዘጋጀት የሚጠቅሙ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመገምገምና በመተንተን ሪፖርት እያዘጋጀ ለመንግሥታዊ፣ ለሌሎች ተጠቃሚ ድርጅቶችና ለግለሰቦች እያሰራጨ ይገኛል፡፡ እነዚህን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የያዙ ጥናቶችን ለማካሄድ በየዓመቱ ከመንግሥት አስፈላጊ የሆነውን የበጀትና የሎጂስቲክስ ድጋፍ የሚደረግለት ሲሆን፤ የጥናቶቹም አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በየጊዜው እያደገና እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በ1995 በጀት ዓመት የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ የሁለት ፕሮጀክቶች ዕቅድ መ/ቤቱ ለመንግሥት አቅርቦና አስፈቅዶ ሥራቸው በተዘጋጀው መረሃ-ግብር መሠረት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በእነዚህ ፕሮጀክቶች የሚካሄዱት ጥናቶች አብዛኛዎቹ አዲሶች ናቸው፡፡ ሆኖም በግብርና ናሙና ቆጠራ የቀጣይ ሥራዎች ፕሮጀክት ስር የሚከናወነው ተግባር በ1994 ዓ.ም በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የገጠር በአርሶ አደሩ አካባቢ የግል ባለይዞታዎች እርሻ፣ የከተሞች አካባቢ፣ የበልግ እርሻዎች፣ እንዲሁም በሰፋፊና መካከለኛ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት ንግድ እርሻዎች መረጃዎችን የማቀነባበርና ሪፖርት የማዘጋጀት ሥራ ግን የነበሩና የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀጣይ ተግባር ሲሆኑ፤ በተጨማሪም በአርብቶ አደር አካባቢ የግብርና የናሙና ቆጠራውን ማካሄድንም ያካትታል፡፡

በመሆኑም በ1995 የሚጠኑ ጥናቶችና ካለፈው ዓመት የተጀመሩ ጥናቶች ሪፖርት ዝግጅት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህም

ሀ. በ1995 በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የሚካሄዱ ጥናቶች

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት /በገጠር/፣
- የግብርና ግብአቶችና አሠራር ( Practices ) ጥናት /በገጠር /፣
- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት/በተመረጡ ገበያዎች/፣
- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በከተማ/፣

- አነስተኛና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በከተማና በገጠር/፣
- የዕደ-ጥበብና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በገጠርና በከተማ/፣
- የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት/በከተማ/፣
- የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ ሙከራ ጥናት/በከተማ/፣
- መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት/በከተማ/፣ እና
- የኢንዴክሶች ዝግጅት ሥራ /በዋናው መ/ቤት/፣ ናቸው።

ለ. በ1995 የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀጣይ ሥራዎች

- የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የሚካሄድ የግብርና ናሙና ቆጠራ ማካሄድ፣ እና
- በአርሶ አደሩ አካባቢ በ1994 የተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት የማዘጋጀት፣ የማተምና የማሰራጨት ተግባርት ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች ለማከናወን በባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1995 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ ሪፖርት በዝርዝር ቀርቧል። በተጨማሪም በሪፓርቱ የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሌሎች ተግባራት እንዲሁም በሩብ ዓመቱ በዕቅድ አፈፃፀሙ ያጋጠሙ ችግሮችና የበላይ አካልን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

በ1995 በጀት ዓመት የሚጠኑ አብዛኛዎቹ ጥናቶች ሁሉም የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ ሲሆኑ፤ በሁለቱም ፕሮጀክቶች ስር ለማካሄድ በዕቅድ የተያዙ ጥናቶችን በተመለከተ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተከናወኑ ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል።

### 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

### 2.1.1 ዓመታዊ የግብርና ናሙና ጥናት

ሀ. የሰብል ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- በ1995 ዓ.ም ከመስከረም ወር ጀምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ መጠይቆች፣ የመረጃ

ሰብሳቢዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል::

- ለዚሁ ጥናት ከመስክ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ኤዲቶ፣ ኮድና ቬሪፋይ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ኮድ ቡኮች ተዘጋጅተው በበቂ ኮፒ እንዲባዙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል::

- ለ1995 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከመስክ በመሰብሰብ ላይ ስለሚገኙ መረጃዎች የአሰባሰብ ሂደትና የመረጃዎቹን ጥራት በተመለከተ ከዋናው መ/ቤት ባለሙያዎች ተልከው ቁጥጥር አድርገው ተመልሰዋል::

ለ. <u>የእርሻ መሬት ስፋት መረጃን በተመለከተ</u>

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው የመኸር ወቅት ጊዜያዊ ሰብሎችን በተመለከተ በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትና ምርት መጠን (Preliminary Results on Area, Production and Yield of Crops) የመጀመሪያ ውጤት ተዘጋጅቶ በመገምገም ላይ ይገኛል::

- የ1994 ዓ.ም ግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው በቋሚ ሰብሎች የተያዙ የመሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ ቬሪፊኬሽንና የኤዲቲንግ ሥራ ተጠናቆ የቆጠራውን ውጤት የያዙ ሠንጠረዦች በመውጣት ላይ ይገኛሉ::

ሐ. <u>የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ (Farm Management Practices) መረጃን በተመለከተ</u>

- የ1993 ዓ.ም የበልግ ወቅት የእርሻ አጠቃላይ ሁኔታን (Farm Management Practices) የሚያሳዩ መረጃዎች በ1994 ዓ.ም በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ ሥራ መደራረብ ምክንያት ቅንብሩ እንዲዘገይ ከተደረገ በኋላ በዚህ በጀት ዓመት ሪፖርቱ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል::

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ አንዱ የሆነው የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ቀደም ብለው በተዘጋጁ የቆጠራውን ውጤት በሚያሳዩ

ሠንጠረዦች ላይ ወጥተው የመረጃው አስተማማኝነትና መጣጣም እየተመረመረ ሲሆን፣ አዲስ በተዘጋጀው የቆጠራውን ውጤት የሚያቀርብ ሠንጠረዥ የማዋሃዱ ሥራ በባለሙያዎች ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነው።

መ. <u>የቤት እንስሳት፣ ዶሮ ሀብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ</u>

የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የቤት እንስሳት፣ ዶሮ ሀብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ ለገጠሩ አካባቢ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል። በመሆኑም የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የትግራይና የአፋር መረጃዎች ተቀነባብረው ውጤቱ በመምሪያው ባለሙያዎች በመገምገም ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ወደ ተሻሻለው የቆጠራውን ውጤት የሚያሳይ ሠንጠረዥም የመለወጡ ተግባር በቅርቡ ይጀምራል። የአማራ ክልል መረጃ የማጥራት ተግባር እየተካሄደ ሲሆን፣ የኦሮሚያ መረጃ ደግሞ ወደ ኮምፒውተር በመግባት ላይ ይገኛል።

ሠ. <u>የመሬት አጠቃቀም (Land use) መረጃን በተመለከተ</u>

የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የመሬት አጠቃቀም መረጃ በኮምፒውተር የማቀነባበሩ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የውጤቱም ትክክለኛነትና አስተማማኝነት በባለሙያዎች እየተገመገመ ይገኛል። በተጨማሪም ይህን መረጃ በተመለከተ በተሻሻለውና የቆጠራውን ውጤት ለማቅረብ በተዘጋጀው ሠንጠረዥ የማዋሃድ ሥራ በቅርቡ ይጀመራል።

ረ. <u>ሌሎች የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃዎችን በተመለከተ</u>

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የምርት አጠቃቀም፣ የእርሻ መሣሪያዎችና ማከማቻዎች እንዲሁም ሌሎች መረጃዎች የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራዎች በመገባደድ ላይ ይገኛሉ።

- በ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ መሠረት ለሚዘጋጀው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የቆጠራ ውጤትን በተመለከተ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በተሰጣቸው ርዕሶች ላይ የሪፖርት ዝግጅት ተጀምሯል።

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የከተማ አካባቢ ቆጠራ መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ሰ. ሌሎች ሥራዎችን በተመለከተ

ከFAO እና መሰል ድርጅቶች ለሚቀርብ የመረጃ ጥያቄዎች አስፈላጊውን መረጃና የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

## 2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት

### 2.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶችን ሥራ በተመለከተ

ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት

- ከመስከረም ወር 1994 ዓ.ም ያሉ መረጃዎች የዳታ ኢንትሪና የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቅቆና ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሕትመት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

- ከጥር ወር 1994 ዓ.ም እስከ መጋቢት ወር 1994 ዓ.ም ድረስ ያሉት መረጃዎች የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ ለዳታ ክሊንግ ሥራ እየተዘጋጀ ሲሆን፣ ከሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም እስከ ሐምሌ ወር 1994 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል፡፡

- የ1995 በጀት ዓመት የሚያገለግለው መጠይቅ ታትሞ እንዲሰራጭ የተደረ ሲሆን፣ መረጃውም ከመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል፡፡

ለ. የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ዝግጅት

- የ1993 ዓ.ም መሠረት የሚያደርገው የሸማቶች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ

– የ11 ክልሎች/ መስተዳድሮች እና በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚያዚያ ወር 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር 1994 ዓ.ም ድረስ ያሉትን የሸማች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዞች ስሌት ተከናውኖና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

– የሐምሌ ወር 1994 ዓ.ም እና የነሐሴ ወር 1994 ዓ.ም ጠቋሚ አሃዝ ተዘጋጅቶ ለሕትመት ተልኳል፡፡

- የአዲስ አበባ ከተማ የመስከረም ወር 1994 ዓ.ም ጠቋሚ አሃዝ ለሕትመት ተዘጋጅቷል።

## 2.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት

### 2.3.1 የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ ጥናት

#### ሀ. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት

- በመጋቢት ወር 1994 ዓ.ም የተሰበሰበው ለ1993 ዓ.ም የዘርፉ ጥናት መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የሠንጠረዥ ቅንብር ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት ቀርቧል።

- በ1995 ዓ.ም ሊካሄድ ለታቀደው የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት የሥራ ክንውኝ የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ግምት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ የመጠይቆቹ ክለሣ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

#### ለ. የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት

- በ1995 ዓ.ም ሊካሄድ ለታቀደው የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት /በገጠርና በከተማ/ የሥራ ክንውኝ የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ግምት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ የመጠይቆች ክለሣ ሥራ በመካሄድ ላይ ነው።

- ለዚሁ ጥናት የሚሆነው የፍሬም ዝግጅት በሦስት ወረዳዎች ላይ የሙከራ ጥናት እየተካሄደ ይገኛል።

#### ሐ. የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃን በተመለከተ

የዘርፉ የ1993 ጥናት መረጃ ተሰብስቦና ተጠናቆ ለሕትመት ቀርቧል።

#### መ. የጎጆ/ዕደጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት

በገጠር ለሚካሄደው የጎጆ/ዕደ ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት መጠይቅ ታትሞ ለቅ/ጽ/ቤቶች የተላከ ሲሆን፣ ሌሎችም ሥራውን በመስክ ለማከናወን የሚያስፈልጉ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት ተከናውነዋል።

ሠ. <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ኢንዴክስ ሥራን በተመለከተ</u>

የ1993 ዓ.ም የሚያካትተው የኢንዴክስ ሥራ የመረጃ ቅንብር ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል።

ረ. <u>የውጭ ንግድ፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ</u>

- የ1993/94 ዓ.ም መጽሔት ዝግጅት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።
- እ.ኤ.አ የ2000 እና የ2001 የውጭ ንግድ መረጃ ሙሉ በሙሉ ተሰብስቦና የመረጃ ቅንብር ሥራው ተከናውኖ ለሕትመት ቀርቧል።

ሰ. <u>መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ (Informal Sector/ ጥናትን በተመለከተ</u>

በ1995 በጀት ዓመት ሊካሄድ የታሰበውን የመደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ /Informal Sector/ ጥናት የሥራ ክንውኝ የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ግምት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ መጠይቅና የአሞላል መመሪያ የክለሣ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

ሸ. <u>የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናትን በተመለከተ</u>

በ1995 ዓ.ም ሊካሄድ የታሰበው የአከፋፋይ ንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት የሥራ ክንውን የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ፍላጎት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ መጠይቅና የአሞላል መመሪያ የክለሣ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

2.4 <u>የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

2.4.1 <u>የትምህርት፣ ባህልና ስፖርት፣ ሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ</u>

ሀ. <u>የባሕልና ስፖርት ስታቲስቲክስ</u>

የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን የስፖርት መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማጠናከር እንዲረዳ ሙያዊ እገዛ እንዲደረግለት በጠየቀው መሠረት አስፈላጊው ትብብርና እገዛ ተደርጓል።

ለ. <u>የትምህርት ስታቲስቲክስ</u>

የ1994 ዓ.ም የትምህርትና የባሕል መረጃዎችን ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ለማግኘት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል።

ሐ. <u>የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ</u>

- ለ1994 ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት ቡድኑን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲቻል የመረጃ ምንጭ ለሆኑ መ/ቤቶች የሚላኩ ሠንጠረዦች በዝግጅት ላይ ይገኛሉ።

- የኤች አይቪ ኤድስን ለመቆጣጠርና ለመገምገም በተዘጋጀው ዶክመንት ላይ ለመወያየት በተካሄደ አውደ ጥናት መ/ቤቱ የተሣተፈ ሲሆን፣ በግብረ-ሃይል አባልነትም ተመርጧል። እንዲሁም ወጣቱን በሚመለከት የፖሊሲ ማዕቀፍ (framework) ለማዘጋጀት በአገር አቀፍ ደረጃ በተቋቋመው ግብረ-ሃይል መ/ቤቱ በአባልነት እየሰራ ይገኛል።

2.4.2 <u>የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ</u>

- በ1993 ዓ.ም ተካሂዶ የነበረው የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናት " Report on Child Labour Survey 2001" ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ የታተመ ሲሆን፣ ሪፖርቱን ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት እንዲቻል የሥራው ተባባሪ /partner/ ለሆነው ለሠራተኛና ለማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለዓለም ሥራ ድርጅት /ILO/ ሪፖርቱ ተልኮ አስተያየትና ስምምነታቸው እየተጠበቀ ነው።

- ይህንኑ ጥናት በሴሚናር መልክ ለተጠቃሚዎች ለማስተዋወቅ እንዲቻል በሴሚናሩ የሚቀርቡ የመግለጫዎችና የግራፎች ረቂቅ ተዘጋጅቷል። እንዲሁም በጥናቱ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ሌሎችም በዶክመንት መልክ እንዲቀመጡ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

### 2.4.3 ተከታታይ የሰው ኃይል ጥናትን በተመለከተ (Current Employment Survey)

ተከታታይ የሆነ የሥራ ሥምሪት መረጃን ለማመንጨት በዚህ ዘርፍ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የመረጃ ፍላጎትና ክፍተቱን ለማጥበብ ለሚደረገው ጥናት ዝግጅት እየተካሄደ ሲሆን፣ ለጥናቱ እንዲረዳ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ በጥናቱ ሊሰበሰቡ የሚችሉ መረጃዎችን... ወዘተ የሚገልጽ ጽሑፍ /Proposal/ እየተዘጋጀ ይገኛል::

ሠንጠረዥ 1 በ1995 1ኛ ሩብ ዓመት የጥናቶች የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም (በመቶኛ)

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1994 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የ1995 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | **የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም** | | | | | |
| 1.1 | የ1995 የግብርና ናሙና | | | | | |
| | • የግብርና ሰብል ትንበያ ጥናት፣ እና | አዲስ | 9.60 | 50.4 | 50.4 | 100 |
| | • የግብርና ግብዓቶች አሠራር ጥናት፣ | አዲስ | 9.60 | 50.4 | 50.4 | 100 |
| 1.2 | የትላልቅና የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ.ጥናት 1993 | ነባር | 81 | 14.00 | 14.00 | 100 |
| 1.3 | የጎጆ /ዕደጥበብና የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት/በገጠር/ | አዲስ | 15 | 10.3 | 10.3 | 100 |
| 1.4 | የጎጆ /ዕደጥበብና የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት/በከተማ/ | አዲስ | 15 | 12.27 | 8.18 | 67* |
| 1.5 | የአከፋፋይና የአገል. ሰጪ. ንግድ ድርጅቶች ጥናት | አዲስ | 15 | 7.98 | 5.32 | 67* |
| 1.6 | መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት | ኢዲስ | 15 | 6.44 | 4.30 | 67* |
| 1.7 | የዋጋዎች ጥናት | | | | | |
| | • የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር፣ እና | አዲስ | 9.46 | 21.95 | 21.95 | 100 |
| | • የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ፣ | አዲስ | 15 | 17.93 | 17.93 | 100 |
| 1.8 | የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ ሙከራ ጥናት | አዲስ | - | 2.55 | 2.55 | 100 |
| 2 | **የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች** | | | | | |
| 2.1 | የ1994 ዓ.ም ግብርና ቆጠራ መረጃ ማቀነባበር ሥራ | ነባር | | | | |
| | • የዋናው መኸር ወቅት ግብርና ናሙና ቆጠራ፣ | " | 6.9 | 6.99 | 17.50** | - |
| | • የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች፣ | " | 65 | 6.81 | 14.00** | - |
| | • የከተማ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ | " | 67.41 | 7.53 | 7.00 | 93 |
| | • የበልግ ወቅት፣ እና | " | - | - | - | - |
| | • የሰፋፊ እርሻዎች | " | - | - | - | - |
| 2.2 | የአርብቶ አደሩ (አፋርና ሱማሌ) ግብርና ቆጠራ | አዲስ | 8.42 | 3.29*** | - | - |

* በጀቱ የተፈቀደው ዘግይቶ ስለነበር ነው::

** ከታቀደው በላይ የተከናወነው በርካታ ኮንትራት ሠራተኞችን በመቅጠርና በሁለት ፈረቃ በማሰራታችን ነው::

*** በክልሉ በተከሰተው የአየር መዛባት ምክንያት ሥራውን ለመቀጠል ወይም ለማቋረጥ ከክልሉ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ለማድረግ በዕቅድ ስለተያዘ የዝግጅት ሥራው ተቋርጧል::

## 3. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅት፣ መዛግብት አያያዝና ስታንዳርድስ

በዚህ ክፍል በየዓመቱ ለሚካሄዱ የተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችና የአፈጻጸም መመሪያዎች እንዲሁም ለጥናቶች የሚያገለግሉ መጠይቆችና ቅጾች ጥራት፣ ብቃትና ወካይነታቸውን በማረጋገጥ ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል:: በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በክፍሉ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውኗል::

### 3.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ

- ለ1995 የሰብል ትንበያ ጥናት የሚያገለግል ሰርቬይ ዶክመንት ከ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ ውስጥ የእንደገና Sub sample በመውሰድ የናሙና ምርጫ ተካሂዶና ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ውሏል::

- በ1995 ለሚካሄደው የጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ጥናት የሳምፕሊንግ ፍሬም ወቅታዊ /Update/ የማድረግ ሥራ ለገጠሩ የናሙና ምርጫ ተካሂዶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል::

- የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል ለሆነው የመኸር ወቅት መረጃ የማባዣ ወይም /Raising Factor/ እና ውጤቱን የመገምገም ሥራ ተጠናቆ ለሚመለከተው መምሪያ ተሰጥቷል::

- ሰርቬይ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ ለሌሎች መንግሥታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ሙያዊ እገዛ ተደርጓል::

### 3.2 የመዛግብት አያያዝና ስታንዳርድን በተመለከተ

- በመ/ቤቱ ውስጥ የሚካሄዱ ጥናቶች፣ መጠይቆችንና ቅጾችን በመመርመር በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ ለአንድ ጥያቄ የተለያዩ አማራጮችና ኮዶች የተሰጠባቸውን ጥያቄዎችና ጥናቶች በመለየት ልዩነቱን ለማስታረቅ እንዲቻል ዝርዝሩ ለመ/ቤቱ ማኔጅመንት ቀርቧል::

- በጎጆ /ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪና በአነስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናት ውስጥ የሚገኙ ጽንሰ ሃሣቦችን በተመለከተ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር የሚጠቀሙባቸው ጽንሰ ሃሣቦች ተዘጋጅተው ለአስተያየት ቀርቧል።

## 4. የ1994 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ የሚያወጣውንና የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ ነክ ሁኔታዎች የሚገልጹ መረጃዎችን የሚያካትተው የ1994 ዓ.ም ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች እንዲሁም ድርጅቶች በመሰብሰብ ላይ ይገኛል። ይህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያካትት ተደርጎ የሚዘጋጅ ሲሆን፣ እነዚህም

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የውጭ ንግድ መረጃዎች፣
- ዓመታዊ የሀገር ሃብት መረጃዎች
- የመንግሥት ገንዘብ /Public Finance/ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የመድህን /ኢንሹራንስ/መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የስፖርትና ሲኒማ መረጃዎች፣...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 5. ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- ከተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ግለሰብ መረጃ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በመቀበል አስፈላጊውን ስታቲስቲካዊ መረጃና ድጋፍ ተደርጓል።

- በ1995 ዓ.ም ለሚካሄዱ ጥናቶች የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በጥናቱ ላይ ለሚሣተፉና ለሚሰማሩ መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች እንዲሁም የጽ/ቤት አስተባባሪዎችና ስታቲስቲሽያኖችን በማሰልጠንና ከመስከረም ወር ጀምሮ በመካሄድ ላይ ላለው የሰብል ትንበያ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ላይ በመስክ ሥራ ቁጥጥርና ግምገማ ተሳታፊ ሆነዋል።

- መ/ቤቱ ከUSAID በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በአማራ ብሔራዊ ክልል ተደጋጋሚ ድርቅ በሚከሰትባቸው ሦስት ዞኖች ለተመረጡ ሦስት ወረዳዎች ማለትም በደቡብ ጎንደር ላይ ጋይንት ወረዳ፣ በሰሜን ወሎ ጉባላፍቶ ወረዳና በዋግኽምራ ዞን በሰቆጣ ወረዳ ለሚካሄድ ጥናት በናሙና በተመረጡ 75 የቆጠራ ቦታዎች መረጃ ሰብሳቢዎችን በመመልመልና በማሰልጠን አስፈላጊ መረጃ እየተሰበሰበ ይገኛል።

## 6. <u>የማስታወቂያ ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት</u>

- በመ/ቤቱ የተዘጋጁ 79 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔቶች፣ 677 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ፣ 4 የሕዝብና ቤት ቆጠራ፣ 90 የግብርና ስታቲስቲክስ፣ 130 የዋጋ ጥናትና አንድ የኢንዱስትሪ ጥናት በጠቅላላው 981 ሪፖርቶች ለመንግሥት፣ ለአለም አቀፋዊ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የጥናትና ምርምር ማዕከላት እንዲሁም ለግለሰቦች በነፃ ተሠራጭተዋል። እንዲሁም በዚሁ ሩብ ዓመት 93 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔቶች፣ 208 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ፣ 187 የሕዝብና ቤት ቆጠራ፣ 74 የግብርና ስታቲስቲክስ፣ 147 የዋጋ ጥናትና 46 የኢንዱስትሪ ጥናት በጠቅላላው 755 ሪፖርቶች በብር 22,435.95 ሽያጭ ተፈጽሟል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 1,736 ሪፖርቶች ስርጭት ተከናውኗል።

- ለመጀመሪያ ጊዜ ለመ/ቤቱ ልሣን ይሆናል ተብሎ የታሰበው "ዜና ማስባ" ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ ኤዲቶሪያል ኮሚቴ ቀርቧል።

- የመ/ቤቱ ቤተመጻሕፍት ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች፣ ከውጭ ለሚመጡ የውጭ ዜጎችና በጥናትና ምርምር ሥራ ላይ ለሚሣተፉ ግለሰቦችና መረጃ ፈላጊዎች ያለማቋረጥ የንባብና የመጽሐፍ ውሰት አገልግሎት ተሰጥቷል።

- እንዲሁም ወደፊት መ/ቤቱ ለሚያዘጋጃቸውና ለሚያሣትማቸው የውስጥ የዜና መጽሔቶች፣ ቡሮሹሮች፣ ቡለቲኖች... ወዘተ የማማከር ሥራዎች ላይ የሚሣተፈው የኤዲቶሪያል ኮሚቴ መተዳደሪያ መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለቦርዱ ቀርቧል፡፡

## 7. የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት

- በ1994 ዓ.ም የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሦስት የነገረፈጅ መደቦች እንዲፈቀዱለት በጠየቀው መሠረት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በኮሚሽኑ ተፈቅዷል፡፡

- የመ/ቤቱ የሥራ ሽፋን እየጨመረ በመምጣቱ አንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች ካላቸው የቆዳ ስፋትና የቦታ ርቀት አንፃር ሁሉንም የቆጠራ ቦታዎች በአንድ የጥናት ወቅት በተደጋጋሚ ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል፡፡ በመሆኑም ችግሩን በተወሰነ ደረጃ ለመቅረፍ እንዲቻል ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ በአምስት ጽ/ቤት የነገሌ አካባቢን ሲሸፍን የነበረ ሲሆን ችግሩን ለማቃለል በነገሌ፣ የሶዶ አካባቢን የአርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት ሲሸፈን የነበረውን ችግሩን ለማቃለል በሶዶ፣ እንዲሁም የሽሬን አካባቢ በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ሲሸፈን የነበረውን በሽሬ ተጨማሪ ጽ/ቤቶች ተከፍተው ሥራ እንዲጀምሩ የተደረገ ሲሆን፤ ለጽ/ቤቶቹ የኃላፊና ሌሎች የስምንት ሥራ መደቦች እንዲፈቀድላቸው ጥያቄው ለሲቪል ሰርሲቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ምላሹን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

- በ1995 የትምህርት ዘመን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተው የማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም እንዲከታተሉ አንድ ሠራተኛ በዲሞግራፊ፣ ሁለት ሠራተኞች በስታቲስቲክስ እና ሦስት ሠራተኞች በኢኮኖሚክስ ትምህርት ዘርፍ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎላቸው ትምህርት ጀምረዋል፡፡ እንደዚሁም ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ከቆዩ ሠራተኞች ውስጥ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አንድ ሠራተኛ በዲሞግራፊ እንዲሁም አንድ ሠራተኛ በስታቲስቲክስ የማስተርስ ዲግሪ አግኝተው መ/ቤቱን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

## 8. የኦዲት አገልግሎት

- ከቅ/ጽ/ቤቶች ሊወራረዱ ከሚመጡ ሰነዶች መካከል የነዳጅ ወጪዎችን ለመ/ቤቱ መኪኖች አገልግሎት የዋለ መሆኑን ከኪሎ ሜትር ካርድ ጋር በማገናዘብና በመቆጣጠር ደረሰኞች እንዲወራረዱ አድርጓል።

- የጎንደርና የአርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል አግኝተው ትምህርት ቤት በመግባታቸው፣ እንዲሁም የጅጂጋ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ወደዋናው መ/ቤት በመምጣታቸው ሲያንቀሳቅሱት የነበረውን የመንግስት ገንዘብ በመመርመር በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቱ ኦዲተሮች አማካይነት ርክክብ እንዲያደርጉ ተደርጓል።

## 9 ሕግ አገልግሎት

- የመ/ቤቱ ሠራተኞች በነበሩት ጊዜ የመንግሥትን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ በመ/ቤቱ በተሰጣቸው የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት በጉድለት ከሚታየው ብር 21,573.27 ውስጥ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብር 6,207.00 ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል።

- በመ/ቤቱ ሠራተኞች የነበሩ መ/ቤቱ የሚፈልግባቸውን በጠቅላላ ብር 77,030.66 ገቢ እንዲያደርጉ ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት አቅርቦ ውሣኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ጊዜያት በሰዎች ላይ ላደረሱት ጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው በጠቅላላው ብር 404,840.20 በሚመለከተው ፍርድ ቤት በኩል አቅርበው እየታየላቸው ይገኛል።

## 10 ፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት

- በ1995 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መረሃ-ግብሩ መሠረት የገንዘብ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል አስተላልፏል።

- የመ/ቤቱን ወርሃዊ የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል አስተላልፏል።

- ከዚህ ቀደም ተዘጋጅቶ የነበረውን የመ/ቤቱን የአምስት ዓመት የስታቲስቲክስ ጥናት ቅደም ተከተል ፕሮግራም ከሚመለከታቸው መምሪያዎች ጋር በመሆን የማሻሻል ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል።

## 11. <u>የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና</u>

### 11.1 <u>የሰው ኃይልን በተመለከተ</u>

በ1995 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,513 ቋሚና 2,213 የኮንትራት በጠቅላላው 3,726 ሠራተኞች ነበሩ። ከነዚህ ቋሚ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ውስጥ 77 ሠራተኞች አዲስ ወደ ተቋቋመው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የተዛወሩ፣ 9 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የለቀቁ፣ 12 ሠራተኞች በሞት የተለዩ እንዲሁም 7 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ ሲሆን የ27 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል። በሌላ በኩል ከነበሩት የኮንትራት ሠራተኞች ውስጥ 1,894 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 21 ሱፐርቫይዘሮች፣ 58 የዳታ ኢንትሪና የኤዲቲንግ ሠራተኞች፣ 48 የአስተዳደርና 107 ሾፌሮች በጠቅላላው 2,128 የኮንትራት ሠራተኞች ሲቀጠሩ 1,818 የኮንትራት ሠራተኞች ደግሞ ከሥራ ተሰናብተዋል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት 3,958 ሲሆን፣ ከእነዚህ ሠራተኞች ውስጥ 1,435 ቋሚና 2,523 ደግሞ ኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። በመጀመሪያው ሩብ ዓመት መጨረሻ ያለው የመ/ቤቱ ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2 <u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቁጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,513 | 2,213 | 3,726 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 27 | 2,128 | 2,155 |
| 3 | በጡረታ የተገለሉ | (7) | - | (7) |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (9) | (1,818) | (1,827) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (12) | - | (12) |
| 6 | ወደ ሌላ መ/ቤት የተዛወሩ | (77) | - | (77) |
| ድምር | | 1,435 | 2,523 | 3,958 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ወይም በሥራ መደብ ሲተነተን 105 ፕሮፌሽናል፣ 896 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 434 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው:: የእነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1.108 ወንዶች /77.2 በመቶኛ/ ሲሆን 327 ሴቶች /22 በመቶ/ ናቸው::

ሠንጠረዥ 3 <u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ</u>

| | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፆታ | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ጠቅላላ ድምር |
| ወንድ | 88 | 793 | 227 | 1,108 | 23 | 2,004 | 149 | 2,176 | 3,284 |
| ሴት | 17 | 103 | 207 | 327 | 2 | 332 | 13 | 347 | 674 |
| ድምር | 105 | 896 | 434 | 1,435 | 25 | 2,336 | 162 | 2,523 | 3,958 |

## 11.2 <u>የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሠራተኞችን የሥራ ብቃት ለማሣደግና የተሻለ አቅም ለመፍጠር በየዓመቱ በተለያዩ የሙያ ዓይነቶች ሥልጠና እንዲያገኙ የሚያደርግ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል::

ሀ. 1995 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ስር ለሚካሄዱ በገጠር የግብርና ናሙና ጥናቶች፣ ለአምራቾች ዋጋ ጥናትና፣ ለዕደ ጥበብ/ ጎዶ ኢንዱስትሪ ጥናት በዋናው መ/ቤት ለ55 ባለሙያዎች ከሐምሌ 5 ቀን 1994 እስከ ሐምሌ 13 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ የአሠልጣኞች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም ለ2,324 መረጃ ሰብሳቢዎች፣ ለ426 ተቆጣጣሪዎችና ለ78 ስታቲስቲሽያኖችና አስተባባሪዎች ከሐምሌ 16 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 28 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷል::

ለ. ለመ/ቤቱ ሠራተኞች አዲስ የወጣውን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ በገጠር ልማት፣ በአቅም ግምባታና በዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ተወያይቶ አንድ አገራዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል:: በዚሁም መሠረት የዋናው መ/ቤት ሠራተኞችን በሁለት በመክፈል ሥልጠናና ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ለ22ቱ ቅ/ጽ/ቤት ሠራተኞች በ8

የሥልጣና ማዕከላት ከላይ በተጠቀሱት ርዕሶች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል።

## 12. የበጀት አጠቃቀም

ለ1995 በጀት ዓመት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት የመደበኛና የካፒታል በጀት በጠቅላላው ብር 48,479,100 የተመደበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም 19,688,300 ብር ለግብርና ናሙና ቆጠራ ቀጣይ ስራዎች 14,138,400 ብር በጠቅላላው ለሁለቱ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ብር 33,826,700 (69.8 በመቶ) የካፒታል በጀትና ብር 14,642,400 (30.2 በመቶ) ለመደበኛ በጀት የሚውል ነው።

### ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

በበጀት ዓመቱ ለመደበኛ ሥራዎች የተመደበውን ብር 14,652,400 በሦስት ዋና ዋና የወጪ አርዕስቶች በመከፋፈል ሥራ ላይ ለማዋል የታቀደ ሲሆን፣ ይኸውም

- ለደመወዝ ............ ብር 12,826,100
- ለውሎ አበል ............ ብር 48,000
- ለሥራ ማስኬጃ ............ ብር 1,768,300 የሚውል ነው።

በ1995 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ማለትም ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ የመደበኛ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነው ብር 3,052,154 ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 3,009,205 ነው። አፈጻጸሙም ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 20.7 በመቶ ሲሆን፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ የገባው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 98.6 በመቶ ነው። ዝርዝሩም በሠንጠረዥ 4 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 4 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የመደበኛ በጀት አፈፃፀም

| በጀት አጠቃቀም | ለ1995 በጀት ዓመት የተፈቀደ | በበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ ገቢ የሆነ | በተይቆ ገቢ ከሆነው ሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት 03 እና 04 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| ደመወዝ | 12,836,100 | 2,869,546 | 2,869,546 | - |
| ውሎ አበል | 48,000 | 4,364 | 4,504 | (140) |
| ሥራ ማስኬጃ | 1,768,300 | 178,247 | 135,155 | 43,089 |
| ድምር | 14,652,400 | 3,052,154 | 3,009,205 | 42,949 |

ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም

በ1995 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች በካፒታል በጀት ብር 33,826,700 ከመንግሥት የተፈቀደ ሲሆን፣ ይኸውም ብር 19,688,300 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የሚውል ሲሆን፣ ቀሪው ብር 14,138,400 ደግሞ በ1994 ዓ.ም በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ በአርሶ አደሩ አካባቢ የተሰበሰበውን መረጃ ለማቀነባበርና ለሪፖርት ዝግጅትና እንዲሁም በ1995 ዓ.ም በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለሚካሄደው የግብርና ቆጠራ ማስፈጸሚያ የሚውል ነው፡፡

ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ለሁለቱ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ በጠቅላላው ብር 7,282,611 ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 6,914,211 እንዲሁም ለግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች ደግሞ ብር 367,400 ወጪ ሆኗል፡፡ ዝርዝሩም በሠንጠረዥ 5 ላይ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 5

## የ1995 ዓ.ም የ1ኛ ሩብ ዓመት የካፒታል በጀት አፈፃፀም

| ተ.ቁ | የበጀት አጠቃቀም | የበጀት ኮድ | ለ1995 ዓ.ም የተፈቀደ በጀት | በሩብ ዓመቱ ተጠይቆ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት /04 እና 05/ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 |
| 1. | ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም | | 19,688,300 | 7,202,614 | 6,914,211 | 288,403 |
| 1.1 | ለሠራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎች | 6110 | 7,333,800 | 2,190,414 | 2,153,136 | 37,278 |
| 1.2 | ለአላቂ ዕቃዎችና መሣሪያዎች | 6210 | 2,939,700 | 845,000 | 648,983 | 196,017 |
| 1.3 | ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርትና..ወዘተ | 6230 | 6,076,000 | 3,506,900 | 3,007,031 | 499,869 |
| 1.4 | ለዕድሣትና ጥገና አገልግሎት | 6240 | 1,908,000 | 519,400 | 849,184 | (329,784) |
| 1.5 | በውል ለሚፈፀሙ አገልግሎቶች | 6251 | 1,280,800 | 140,900 | 254,677 | (113,777) |
| 1.6 | ለአገር ውስጥ ሥልጠና | 6271 | 150,000 | - | 1,200 | (1,200) |
| 2. | የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች | | 14,138,400 | 2,149,390 | 367,400 | 1,781,990 |
| 2.1 | ለሠራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎች | 1110 | 9,566,700 | 1,201,290 | 324,173 | 877,117 |
| 2.2 | ለአላቂ ዕቃዎችና መሣሪያዎች | 6210 | 427,400 | 45,200 | 18,500 | 26,700 |
| 2.3 | ለውሎ አበል፣ ትራንስፖርት... ወዘተ | 6230 | 2,838,300 | 817,900 | 24,727 | 793,173 |
| 2.4 | ለዕድሣትና ጥገና አገልግሎት | 6240 | 299,000 | 35,000 | - | 35,000 |
| 2.5 | በውል ለሚፈፀሙ አገልግሎቶች | 6251 | 1,007,000 | 50,000 | - | 50,000 |
| | ድምር | | 33,826,700 | 9,352,004 | 7,281,611 | 2,070,393 |

## 13. የአገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

### ሀ. የጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

- ለመ/ቤቱ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ ውሣኔ ካገኙ 16 የመስክ ተሽከርካሪዎች ውስጥ 8ቱ በብር 405,000 የተሸጡ ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ ድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ለሚመለከተው መ/ቤት የድጋሚ ጨረታ ማስታወቂያ ተልኳል።
- ለ1995 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ የጽ/መሣሪያና የጽዳት ዕቃዎች ግዢ እንዲሁም የኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ የህትመት ማሽንና የፎቶ ኮፒ ማሽን የጥገና ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪዎች ለተገኙበት የጨረታ ሁኔታ ትንተና (Bid Analysis) እየተከናወነ ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ ማለትም ብቁ ተወዳዳሪ ላልተገኘላቸው ሌላ የድጋሚ ጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ አስፈላጊው መረጃ ለሚመለከተው መ/ቤት ተልኳል።
- መ/ቤቱ ለተገለገለበት የስልክ፣ የመብራት፣ የውኃና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ በወቅቱ እንዲፈፀም፣ እንዲሁም የተለያዩ የቢሮ ውስጥ የጥገና ሥራዎች በየጊዜው በሚመለከታቸው ሠራተኞች እንዲጠገኑና ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።
- መ/ቤቱ ያለው የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ በርካታ በመሆኑ አንዳንድ በአጭር ጊዜና በተደጋጋሚ ብልሽት ለሚያጋጥማቸው የመኪና ዕቃዎች በመ/ቤቱ መካኒኮች ጥገና እንዲደረግላቸው ለማድረግ እንዲቻል በአዲስ አበባ ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ግቢ የጋራዥ ጉድጓድ እንዲሰራ ተደርጎ ሥራው 98 በመቶ ተጠናቋል።
- መ/ቤቱ ላለበት የዶክመንት ማከማቻ ጥበት አገልግሎት የሚውል መጠኑ 12.70ሜ.x 23.20ሜ የሆነ መጋዘን አስገንብቶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የብረት መደርደሪያ እየተገጠመለት ይገኛል።

### ለ. ትራንስፖርትና ጥገና ዋና ክፍል

- የ1995 ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ እንድሣት እንዲያደርጉ በዋናው መ/ቤት የሚገኙ 23 መኪናዎች አስፈላጊው የጥገና ሥራ በመ/ቤቱ

መካኒኮች ተደርጎላቸው፣ የ1995 ከላውዶ (ቦሎ እድሣት) በሚመለከተው መ/ቤት በኩል ተከናውኗል::

- በዋናው መ/ቤት ለሚገኙ የሰርቪስና የመስክ ተሽከርካሪዎች ባለፉት ሦስት ወራት ብር 45,958 ወጪ በማድረግ ነዳጅ፣ ቅባትና እጥበት እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፣ 73 መኪናዎች ቀላልና ከባድ ጥገና በብር 563,526 ተደርጎላቸዋል::

- በ1994 ዓ.ም በግብርና ናሙና ቆጠራ ተግባር ተሰማርተው የነበሩ 7 ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 9 ተሽከርካሪዎች በድምሩ 16 ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን ስለነበራቸው በመድን ድርጅት በኩል አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው አገልግሎት ላይ ውለዋል::

ሐ. <u>የሕትመት ዋና ክፍል</u>

የመ/ቤቱ የሕትመት ዋና ክፍል ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ መስረከም 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጊዜ ውስጥ 2,607,209 ገጽ ያላቸው 34,105 የተለያዩ ዓይነት ጥራዞች አትሞ ለሚመለከተው ክፍል ያቀረበ ሲሆን፣ ከመምሪያዎችና አገልገሎቶች ለሚቀርቡለት የፎቶ ኮፒ አገልግሎቶች ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል::

## 14. <u>በዕቅድ አፈፃፀሙ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች</u>

ሀ. በመ/ቤቱ በየዓመቱ አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን ጥገና በማካሄድ ለረጅም ጊዜ እንዲሰሩ በማድረግ ላይ ይገኛል:: ሆኖም በበጀት ዓመቱ የኢንሹራንስ ሽፋን የሚያገኙት የመንግሥት ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ጊዜያቸው ከ10 ዓመት መብለጥ የለበትም የሚለው የመንግሥት አሠራር የመ/ቤቱን በርካታ ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል:: ይህም ከመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች 15 በመቶውን የሚያጠቃልል ነው:: ስለዚህ የአገልግሎት ጊዜያቸው ከተጠቀሰው ዓመት በላይ ለሆኑና በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ጥቅም በመስጠት ላይ ያሉ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን የሚያገኙበት ሁኔታ ለማመቻቸት መንግሥት ያወጣውን መመሪያ እንደገና መመልከት ወይም ሌላ አማራጭ መፍትሄ እንዲሰጠን እንጠይቃለን::